ጤና ሚኒስቴር - ኢትዮጵያ
MINISTRY OF HEALTH-ETHIOPIA

የዜጎች ጤና ለሃገር ብልጽግና!
HEALTHIER CITIZENS FOR PROSPEROUS NATION!

# አገርአቀፍ የኢትዮጵያ ሆስፒታሎች ጥምረት ለጥራት ፕሮግራም

# የአራተኛው ዙር ማስተባበሪያ እና ማስፈፀሚያ መመሪያ

## ክሊኒካል አገልግሎት ዳይሬክቶሬት

2014 ዓ.ም

EHAQuality

የኢትዮጵያ ሆስፒታሎች ጥምረት ለጥራት
Ethiopian Hospitals Alliance for Quality

## Table of Contents


**መቅድም** ........ i

**ምዕራፍ 1** ........ 1

**መግቢያ** ........ 1

**የነበሩ ልምዶች** ........ 1

**የመመሪያው ክለሳ አስፈላጊነት፡** ........ 2

**ምዕራፍ 2** ........ 3

**የትግበራ ወሰን** ........ 3

**ዋና አላማ** ........ 3

**ዝርዝር አላማዎች** ........ 3

**መርህ** ........ 3

**ምዕራፍ 3** ........ 4

**የጤና ሚንስቴር እና የክልል ጤና ቢሮ የስራድርሻ እና ሃላፊነት** ........ 4

**በጤና ሚኒስቴር ደረጃ** ........ 4

**በክልል ጤና ቢሮ ደረጃ** ........ 5

**ምዕራፍ 4** ........ 6

**የአራተኛው ዙር የጥምረቱ አደረጃጀት እና ቅንጅታዊ አሰራር** ........ 6

**ምዕራፍ 5** ........ 9

**የጥምረቱ 4ተኛ ዙር ወቅት የሚደረጉ አጠቃላይ የድጋፍ ማእቀፎች** ........ 9

**የቴክኒክ ድጋፍ** ........ 9

**የፋይናንስ ድጋፍ** ........ 10

**የማቴሪያል ድጋፍ** ........ 10

**ምዕራፍ 6** ........ 11

**የጥምረቱ 4ኛዉ ዙር የስራ አፈፃፀም ክትትል እና የመረጃ ቅብብሎሽ ስርዓት** ........ 11

**ምዕራፍ 7** ........ 13

**የአራተኛው ዙር ማጠናቀቂያና የእውቅና አሰጣጥ ስርዓት** ........ 13

**አባሪ** ........ 15

## መቅድም

ባሳለፍናቸዉ አመታት በሃገር አቀፍ እንዲሁም በጤናዉ ሴክተር የጤና ተቋማትን የጤና አገልግሎት ተደራሽነት እና ጥራት ለማሻሻል በርካታ የሪፎርም ስራዎች ሲከናወኑ ቆይተዋል፡፡ በመጀመሪያዉ የጤናዉ ዘርፍ የትራንስፎርሜሽን እቅድ ወቅት በሃገር አቀፍም ሆነ በዓለም አቀፍ ደረጃ የተቀመጡ በርካታ ግቦችን ለማሳካት ተችሏል፡፡ ይሁን እንጂ የተገኙ አፈፃፀሞች ላይ ክፍተት የታየባቸዉን ተግባራት እና በዘላቂ ልማት የተቀመጡ ግቦችን ለማሳካት በሁለተኛዉ ዙር የትራንስፎርሜሽን እቅዳችን አዳዲስ አጀንዳዎች እና በርካታ የማስፈፀሚያ ስልቶች በጋራ ተነድፈዉ ወደስራ ተገብቷል፡፡ የኢትዮጵ ሆስፒታሎች ጥምረት ለጥራት ፕሮግራምም ከ 2004ዓ/ም ጀምሮ ሲተገበሩ ከቆዩ የማሻሻያ ፕሮግራሞች ዉስጥ የሚጠቀስ ነው፡፡

የጥምረቱ ዋና ዓላማም በየ2 ዓመቱ የተለያዩ የትኩረት መስኮችን በመምረጥ በሆስፒታሎ በተናጠል እና በክላስተር እንዲተገብሩ በማስቻል፤ ተቋማት እርስ በእርሳቸዉ እንዲማማሩ፤ እንዲደጋገፉ እና ልምዳቸዉን በመለዋወት የሚሰጡትን የጤና አገልግሎት ማጠናከር ላይ ያተኮረ ፕሮግራም ነዉ፡፡ በዚህም ባሳለፍናቸዉ ዓመታት 3 የትኩረት መስኮች የተጠናቀቁ ሲሆን በተመረጡ የትኩረት መስኮች የተሻለ አፈፃፀም ያስመዘገቡ ሆስፒታሎች እዉቅና እንዲያገኙ በማድረግ በርካታ ለዉጦች እና ልምዶች ተመዝግበዋል፡፡

ይሁን እንጂ የጋራ የቅንጅት ስራዎቻችን፤በተቋማት ድጋፍ አሰጣጥ፤በየደረጃዉ ተጠያቂነትን በማስፈን እና በመረጃ ላይ የተመሰረተ ዉሳኔ በመስጠት ሂደት ጎልተዉ የሚጠቀሱ ችግሮች በመኖራቸዉ እነሱን ለመፍታት እና ጥምረቱን የበለጠ ለማጠናከር በያዝነዉ ዓመት የጠቋማትን አገልግሎት ተገልጋ ተኮር፤በሙያዊ ሰን ላይ የተመሰረተ፤ እንዲሆን የሚያስችል የ4ኛዉን ዙር በመረጃ ላይ የተመሰረት የጤና አገልግሎት ክብካቤ የትኩረት መስክ ተቀርፆ በየደረጃዉ ባሉ አደረጃጀቶች በተቀመጠዉ የክትትል እና ድጋፍ ስረዓት በሆስፒታሎቻችን ለማስፈፀም በሚደረገዉ የጋራ ጥረት የተሻለ የጤና አገልግሎት ለዉጥ እንደምናስመዘግብ የሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ሙሉ እምነት ነዉ ፡፡

## ምዕራፍ 1

## መግቢያ

መንግስት የዜጎቹን ጤና ለማበልፀግ እና በጤና አገልግሎት አሰጣጥ የተገልጋዩን ፍላጎት ለማርካት በርካታ የአገልግሎት ማሻሻያ ሪፎርሞችን እየተገበረ ይገኛል፡፡ በሃገር አቀፍ ደረጃም የጤናዉ ሴክተር ግቦችን ለማሳካት ከተቀመጡ የሪፎርም ስራዎች መካከል የኢትዮጵያ ሆስፒታሎች ጥምረት ለጥራት ፕሮግራም አንዱ ሲሆን የጤና አገልግሎት ጥራት እና ተደራሽነትን ለማሻሻል ከ2004 ዓ/ም ጀምሮ እየተተገበረ ይገኛል፡፡

የሆስፒታሎች ጥምረት ለጥራት ፕሮግራም የራሱ አደረጃጀት ያለዉ እና በየ2 ዓመቱ በተመረጡ የትኩረትመስኮች ላይ በሆስፒታሎች መካከል እርስ በርስ የመማማር፣ የመተባበርና የመደጋገፍ መርሆች የተከተለ በጤና ሚኒስቴርና በክልል ጤና ቢሮዎች አስፈጻሚነት የሚተገበር ሲሆን በሁሉም ደረጃ ወቅቱን የጠበቀ ድጋፍና ክትትል፣ የአፈፃጸም ግምገማና የማሻሻያ ግብረመልስ እየተሰጠ የትኩረት መስኩ ከመጠናቀቁ በፊት ምዘና እየተደረገ የተሻለ አፈፃፀም ያስመዘገቡ ሆስፒታሎች፣ ጥምረቶች/Cluster/ እና ክልሎች የማበረታቻ እዉቅና እንዲያገኙ የሚያስችል ፕሮግራም ነዉ፡፡

## የነበሩ ልምዶች

ከዚህ ቀደም በተተገበሩት 3 የሆስፒታሎች ጥምረት ለጥራት ፕሮግራም የትኩረት መስኮች በሆስፒታሎች፣ በክላስተር፣ በክልል እንዲሁም በሃገር አቀፍ ደረጃ የአገልግሎት ጥራት እና ተደራሽነትን በማሻሻል፤ ጤናማ የሆነ የዉድድር መንፈስ በመፍጠር፤ እርስ በእርስ በመማማር፣ መልካም ተሞክሮዎችን በማስፋት፣ የሰውሃይልን ጨምሮ በተለያዩ ግብዓቶች በመደጋገፍ በርካታ ለዉጦች ተመዝግበዋል፡፡ በአፈፃፀማቸዉ ሞዴል የሆኑ ተቋማት እዉቅና እንዲገኙ በማድረግ በርካታ ልምዶች ተገኝተዋል፡፡ ይሁን እንጂ በቅንጅታዊ አሰራር፣ ተጠያቂነትን በመፍጠር፣ ልዩ ልዩ የባለድረሻ አካላትን በማሳተፍ እንዲሁም በየደረጃዉ ያሉ አካላት ፕሮግራሙን በባለቤትነት እንዲመሩት ከማስቻል አንፃር ክፍተቶች ነበሩ፡፡

ባለፉት 3 ዙር የትኩረት መስኮች (የደንበኞች እርካታን ማረጋገጥ፣ የእናቶች እና የህፃናት ጤና አገልግሎት ጥራት ማረጋገጥ፣ ፅዱና ምቹ ደህንነቱ የተረጋገጠ ጤና ተቋም መፍጠር እንዲሁም ንፅህናዉና ወቅቱን የተጠበቀ አገልግሎት ለተቋማት ሽግግር) የትግበራ ሂደት የሆስፒታሎች ቁጥር ከጊዜ ወደጊዜ በመጨመሩ ለምዘና እና ለእዉቅና በእጩነት የሚቀረቡ ሆስፒታሎች ቁጥር በተመሳሳይ እያደገ መጥቷል፡፡ በተመሳሳይ ጥምረቱን

ለማጠናከር የፋይናንስ ድጋፍ አስፈላጊ በመሆኑ ባለፉት 12 ዓመታት ከሩብ ቢሊየን ብር በላይ ለድጋፍ ስራዎች እና ለሆስፒታሎች ማበረታቻነት እንዲዉል ተደርጓል፡፡

## የመመሪያው ክለሳ አስፈላጊነት፡

ባሳለፍናቸዉ 3 የጥምረቱ ዙሮች የተጠናቀቁ የትኩረት መስኮች አመርቂ ውጤቶች እና ልምድ የተገኘባቸው ነበሩ፡፡ በተለይ በጥምረቱ ሆስፒታሎች መካከል በተፈጠረዉ መማማር ፣ መደጋገፍ እንዲሁም በጋራ ችግሮችን የመለየት የመተንተን እና የመፍታት ልምዶቸን በማዳበር የህክምና አገልግሎት አሰጣጥ ከማሻሻል አንፃር ብዙ ለውጦች ታይተዋል፡፡ ይሁን እንጂ ጥምረቱን በተቀናጀ እና ውጤታማ በሆነ መልኩ በሀገር አቀፍ ደረጃ ለማስተግበር የማስፈፀሚያ መመሪያው ብዙ ጉድለቶች ነበሩት፤ ለአብነትም መመሪያው የጥምረቱን የትኩረት አቅጣጫ ከግምት ውስጥ ያላስገባ እና ወጥነት የጎደለው ከመሆኑም በላይ አስፈላጊ የሚባሉ ዝርዝር የስራ ሃላፊነቶችን ፣ አሰራሮች እንዲሁም የፕሮጀክቱ አዘጋግ/የሽልማት እና የእውቅና ስርዓት በተመለከተ አንዳንድ ጉድለቶች ታይተውበታል፡፡

በመሆኑም ከላይ በተጠቀሱት ዋናዋና ምክንያቶች ፣ እንዲሁም የጥምረቱን የአራተኛው ዙር የትኩረት አቅጣጫ ልዩ ሁኔታዎችን ከግምት ውስጥ በማስገባት እና የጤና ሚንስትር የሆስፒታሎችን አገልግሎት ለማሻሻል ከሚተገብራቸው ስትራቴጂክ ፕሮግራሞች አንፃር ነባሩን የማስፈፀሚያ መመሪያ በአዲስ መልክ ሙሉ በሙሉ መከለስ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ መመሪያው ተከልሷል፡፡

## ምዕራፍ 2

### የትግበራ ወሰን

ይህ መመሪያ ለአራተኛው ዙር የኢትዮጵያ ሆስፒታሎች ጥምረት ለጥራት ፕሮግራም በተመረጡ የትኩረት ማእከል በሆኑ የህክምና አገልግሎቶች ለማሻሻል የሚያግዙ ስትራቴጂካዊ ስልቶችን በተቀናጀ፣ ወጪ ቆጣቢ እንዲሁም ዉጤታማ እና ተጠያቂነት ባለዉ መልኩ ለማስተግበር ታስቦ የተዘጋጀ ነዉ። መመሪያው በዋናነት በፌደራል እና በክልል ጤና ቢሮ ስር የሚተዳደሩ ሆስፒታሎች ላይ ተፈፃሚ የሚሆን ሲሆን የትግበራ ግዜው ከሀምሌ 2013 እስከ ሰኔ 2015 ዓ/ም ይሆናል።

### ዋና አላማ

የዚህ መመሪያ ዋና አላማ በ4ኛ ዙር የኢትዮጵያ ሆስፒታሎች ጥምረት ለጥራት (EHAQ) ፕሮጀክት (መረጃን መሠረት ያደረገ የህክምና አገልግሎት) ላይ ለሚሳተፉ ሆስፒታሎች እና ባለድርሻ አካላት የፕሮጀክቱን አተገባበር በተመለከተ አጠቃላይ የአፈፃፀም እና የቴክኒክ መመሪያን መስጠት ነው።

### ዝርዝር አላማዎች

- የፕሮጀክቱን አደረጃጀት እና የባለድርሻ አካላት ዝርዝር የሥራ ድርሻ መወሰን።
- ለተሳታፊ ሆስፒታሎች የሚደረግ የድጋፍ ማዕቀፍ መወሰን።
- የክትትል እና መረጃ ቅብብሎሽ ስርአትን ለመዘርጋት እና ለማሳወቅ ።
- የዙሩን የማጠናቀቂያ እና የዕወቅና አሰጣጥ ስርአትን ለማሳወቅ።

### መርህ

- መረጃን መሰረት ያደረገ ዉሳኔ
- ሙያዊነት/ፕሮፌሽናሊዝም/
- መማማር እና መደጋገፍ
- የግል እና የቡድን ተጠያቂነት
- ወጪ ቆጣቢነት
- ተገልጋይ ተኮር

## ምዕራፍ 3

## የጤና ሚንስቴር እና የክልል ጤና ቢሮ የስራድርሻ እና ሃላፊነት

### በጤና ሚኒስቴር ደረጃ

**የአብይ ኮሚቴ**

**ይህ ኮሚቴ በጤና ሚንስቴር ስር ከሚገኙ የተለያዩ ዳይሬክቶሬቶች፣ ኤጀንሲዎች እና የተለያዩ ለጋሽ ድርጅቶች ከሚውጣጡ ከፍተኛ ተወካዮች የሚዋቀር ሲሆን በሚንስትር ዲኤታ የሚመራ ይሆናል። የሚከተሉትን ተግባራትንም ይፈፀማል:-**

- **በሩብ ዓመት አንድ ግዜ እየተገናኘ ቁልፍ በሆኑ ጉዳዮች ላይ ውሳኔ ያሳልፋል**
- **በተመረጠው የትኩረት መስክ መሰረት የተዘጋጀውን ሰነድ ከጤና ቢሮ ሃላፊዎች ጋር በመሆን ያፀድቃል**
- **በ4ተኛዉ ዙር የትኩረት መስክ ዙሪያ በሚተገበሩ ስራዎች እና በሚጠበቁ ዉጤቶችን በተመለከተ የዉል ስምምነት ሰነድ ከክልል ጤና ቢሮዎች እና ከአስተባባሪ ሆስፒታሎች ጋራ ይፈራረማል**
- **በየደረጃዉ ቅንጅታዊ አሰራር ፣ ባለቤትነት እና ተጠያቂነት እንዲፈጠር ድጋፍ ያደርጋል**
- **በትኩረት መስኩ አፈጻፀም ወቅት የሚያጋጥሙ ቁልፍ ችግሮች ላይ ዉሳኔ ይሰጣል**
- **በቴክኒክ አማካሪ እና በፕሮጀክት አስፈጻሚ ቡድን በሚቀርቡ ምክረ ሃሳብ አማካኝነት ለኢትዮጵያ ሆስፒታሎች ጥምረት ለጥራት ፕሮግራም ተግባራት ማስፈጸሚያ የሚውል ፋይናንስ ላይ ዉሳኔ ይሰጣል**

**የቴክኒክ አማካሪ ኮሚቴ**

**ከጤና ሚንስትር እና ከአጋር አካላት የተዉጣጣ አባላት ያሉት ሲሆን በክሊኒካል አገልግሎት ዳይሬክቶሬት የሚመራ ይሆናል። የሚከተሉትን ተግባራትንም ይፈፀማል:-**

- **የራሱን መግባቢያ ሰነድ ፣ ልዩ ልዩ የፕሮጀክት ሰነዶችን ያዘጋጃል ፤ የፕሮጀክቱን አተገባበር በተመለከተ የማማከር ስራዎችን ይሰራል**
- **በየወሩ የመደበኛ የስራዎች ግምገማ ያከናዉናል**
- **አዳዲስ አጀንዳዎች ላይ እየተወያየ የውሳኔ ምክረ ሀሳብ በማቅረብ በአብይ ኮሚቴ ያስወስናል**

**የፕሮጀክት አስፈጻሚ ቡድን**

**ይህ ኮሚቴ በክሊኒካል አገልግሎት ዳይሬክቶሬት የሚመራ ሲሆን ለ4ተኛው ዙር የተመረጠውን የትኩረት መስክ በመደበኛነት የሚያስፈፅም ቡድን ነዉ። የሚከተሉትን ተግባራትንም ይፈፀማል:-**

- **የተመረጠውን እና የፀደቀውን የትኩረት መስክ ለፈፃሚዎች ያስተዋዉቃል**

- ጥምረቶች/Cluster/ በአዲስ እንዲደራጁ ድጋፍ ያደርጋል
- የፋይናንስ ድጋፎችን ያስተባብራል፤ የቴክኒክ ድጋፍ ያደርጋል
- አስፈላጊ መረጃዎችን ይሰበስባል ፤ ይተነትናል ፤ ግብረ መልስ ይሰጣል
- በጥምረቶች/Cluster/ እና በክልል ደረጃ አፈፃፀም ግምገማ ወቅቱን ጠብቆ እንዲከናወን ድጋፍ ያደርጋል
- የተሻሉ ልምዶች በመለየት ልምዱን ይቀምራል ያሰራጫል

## በክልል ጤና ቢሮ ደረጃ

**አብይ ኮሚቴ**

ይህ ኮሚቴ በክልሉ ነባራዊ ሁኔታ እንዳስፈላጊነቱ ለስራዉ ቀረቤታ ያላቸው ሃላፊዎችን በማካተት በቢሮ ሃላፊ የሚመራ ይሆናል፡፡ የሚከተሉትን ተግባራትንም ያከናውናል፡-

- ባለድርሻ አካላትን ያሳተፈ የፋይናንስ ምንጮችን ያካተተ የማስፈጸሚያ እቅድ ያፀድቃል
- የትኩረት መስኩን ለማስፈፀም የሚስችሉ ዉሳኔዎችን ይወስናል፤ በቂ ክትትል እና ድጋፍ ያደርጋል
- በሃገር አቀፍ ደረጃ የሚወርዱ ማሻሻያዎችን መፈፀማቸዉን ያረጋግጣል፤ቅንጅታዊ አሰራሮችን ያሰፍናል

**የፕሮጀክት አስፈጻሚ ቡድን**

በሜዲካል አገልግሎት ክፍል ሃላፊ ወይም የፈውስ ህክምና አገልግሎት የሚመራ እና በየወሩ መደበኛ ስራዎችን የሚገመግም የስራ ቡድን ነው፡፡ የሚከተሉትን ተግባራትንም ያከናውናል፡-

- የተመረጠውን የትኩረት መስክ ለባለድርሻ አካላት ያስተዋውቃል/ግንዛቤ ይፈጥራል
- በሚንስትር መስሪያ ቤቱ በሚሰጠዉ አቅጣጫ መሰረት የክልሉን የክላስተሮች አደረጃጀት በአዲስ በማደራጀት እና በማፅደቅ ለጤና ሚንስትር ይልካል
- ቴክኒካል ድጋፍ ያካሂዳል፤ ለክላስተር ድጋፍ ማስፈፀሚያ የሚዉል በቂ ፋይናንስ ያስመድባል አጠቃቀሙንም ይከታተላል
- በክላስተር ደረጃ አፈፃፀሞች ወቅቱን ጠብቀው እንዲገመገሙ ይደግፋል
- አስፈላጊ መረጃዎችን በመሰብሰብ በሀገር አቀፍ ደረጃ የሚደረግ የአፈፃጸም ግምገማ ላይ እንዲቀርብ ያደርጋል
- አስፈላጊ ሪፖርቶችን ወቅቱን ጠብቆ እንዲላኩ ይደግፋል
- የመጨረሻ ማረጋገጫ ምዘና በክልል ደረጃ ሲካሄድ ምቹ ሁኔታዎችን ይፈጥራል
- ክልላዊ የእዉቅና ፕሮግራም ያስተባብራል

## ምዕራፍ 4

### የአራተኛው ዘር የጥምረቱ አደረጃጀት እና ቅንጅታዊ አሰራር

የሆስፒታሎች ጥምረት ለጥራት ፕሮግራም በፌደራል፣ በክልል ጤና ቢሮ ፣ በመከላከያ ፣ በፌደራል ፖሊስ እና በግብረሰናይ ድርጅቶች ስር የሚተዳደሩ ሆስፒታሎችን እርስ በእርስ በማስተሳሰር እና በመማማር የሚሰጡትን ህክምና አገልግሎት ውጤቶች ለማሻሻል ያለመ ሲሆን አደረጃጀቱም በአስተባባሪ ሆስፒታሎች ፣ በአባል ሆስፒታሎች እና በሚመሰርቱት ጥምረት ላይ የሚያርፍ ይሆናል፡፡ ለሚመሰረተው ትስስር በተጨማሪም ትስስሩን የሚስተባብሩ ሆስፒታሎች መምረጫ መስፈርት ይኖረዋል፡፡

አስተባባሪ ሆስፒታል

አስተባባሪ ሆስፒታል ማለት ለጥምረቱ አራተኛ ዘር አስተባባሪ ለመሆን በተቀመጠው መስፈርት ተወዳድሮ የተሻለ አፈፃጸም ያለው ሲሆን በጥምረቱ ለተሳሰሩት ሆስፒታሎች በአጀንዳው ዙሪያ እንዲማማሩና እንዲደጋገፉ ምቹ ሁኔታዎች የሚፈጥር ሆስፒታል ነው፡፡

የአስተባባሪ ሆስፒታል መምረጫ መስፈርቶች

- የድንገተኛና ፅኑ ህክምና አገልግሎት፣ የጨቅላ ህፃናት ህክምና አገልግሎት፣ መሰረታዊ የቀዶ ህክምና እንዲሁም ለተመረጡ ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎች ህክምና አገልግሎት የሚሰጥ
- አንፃራዊ የተሻለ የጤና ባለሙያ ስብጥር ያለው
- በክልል ጤና ቢሮዉ (ነባራዊ ሁኔታ እና ልዩ ልዩ መነሻዎች) ተመራጭ የሚሆን
- በትኩረት መስኩ በተመረጡ አራት የህክምና አገልግሎቶች ጥራት ጠቋሚዎች አንፃራዊ የተሻለ አፈፃጸም ያለው

በመከላከያ ፣ በፖሊስ እና በግብረሰናይ ድርጅት ስር የሚተዳደሩ ሆስፒታሎች በአመሰራረታቸው ፀባይ (በተቋቋሙበት አላማ) አማካኝነት የአስተባባሪ ሆስፒታል ሚናን ሙሉ በሙሉ መፈፀም ስለማይችሉ ለአስተባባሪ ሆስፒታል እጩነት መቅረብ አይችሉም፡፡

*ሰንጠረዥ 1. የአስተባባሪ ሆስፒታል መምረጫ መስፈርት ከያዘው ክብደት ጋር*

| ተ.ቁ | መስፈርት | የያዘው ክብደት |
|---|---|---|
| 1 | 4ቱንም አገልግሎት መስጠት (Surgical care, Emergency care, Neonatal care and Outpatient care) | |
| 2 | የአገልግሎት ጥራት (በተመረጡ ጥራት ጠቋሚዎች) የተሸለ አፈፃፀም ማስመዝገብ | |
| 3 | የጤና ባለሙያ ስብጥር | |

| | | |
|---|---|---|
| 4 | በክልል ጤና ቢሮ ያለው ተቀባይነት/ በተለያዩ መነሻዎች እያሰመዘገበ ያለዉ ዉጤት | |
| 5 | እንደ ክልሉ ነባራዊ ሁኔታ ክልሎች ተጨማሪ መስፈርት ማካተት ይችላሉ በተለይ ለጥምረቱ አስፈላጊ በሆኑ ጉዳዮች ላይ | |
| 6 | በጤና ሚኒስቴር ወይም በክልል ጤና ቢሮ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ያለው | |

የአስተባባሪ ሆስፒታል የስራ ድርሻና ሀላፊነት

- የጥምረቱን የጋራ እቅድ እንዲዘጋጅ ያስተባብራል ለክልል ጤና ቢሮ እና ለጤና ሚኒስትር ይልካል
- የመማማር፣ የመደጋገፍ እና የቅንጅት አሰራሮችን እንዲቀረጹና እንዲተገበሩ ያስተባብራል
- በክላስተሩ ካሉ ሆስፒታሎች የተዉጣጣ የክትትልና የድጋፍ ቡድን በማቋቋም፤ የስራ እቅድ በማዉጣት ድጋፍና ክትትል እንዲካሄድ ያስተባብራል
- ወቅቱን የጠበቀ የክላሰተር አፈፃጸም ግምገማ እንዲካሄድ ያስተባብራል
- በጥምረቱ የተሻሉ ልምዶች እንዲቀመሩና አንዲሰፋፋ ያስተባብራል ለክልል ጤና ቢሮና ለጤና ሚንስቴር ይልካል
- የክላስተሩ አፈፃጸም ሪፖርቶችን ወቅቱን ጠብቆ ይልካል

የሆስፒታሎች ጥምረት/ክላስተር

አብሮ የመስራት፣ የመማማር ፣ ጥሩ የሆነ የስራ ትብብርና ጤናማ የሆነ የሥራ ውድድር ላይ የተመሰረተ ሲሆን የሚዋቀረውና የሚፀድቀው በጤና ሚንስትር እና በክልል ጤና ቢሮዎች የጋር ትብብር ነው፡፡ የሆስፒታሎች ጥምረት ሲዋቀር የክልሎችን ነባራዊ ሁኔታ ከግንዛቤ በማስገባትና ከክልል ጤና ቢሮዎች ጋር በመመካከር በአንድ ጥምረት ከ7 እስከ 10 አባል ሆስፒታሎች ያሉት ሆኖ ይደራጃል፡፡ አባላቱም ከአንድ ክልል ውጪ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡

የጥምረቱ የስራ ድርሻና ሀላፊነት

- የጋራ እቅድ እና መግባቢያ ሰነድ በጋራ በማፅደቅ ለክልል ጤና ቢሮና ለጤና ሚንስትር ይልካሉ
- ከጤና ሚንስትር እና ከክልል ጤና ቢሮ የሚወርዱ ጥምረቱን ማሻሻያ ሰነዶች እና ፕሮቶኮሎች ይተገብራሉ
- የቦታ ላይ ድጋፍና ክትትል በማካሄድ እና በዉጤቱ ላይ ተነስተዉ የአፈፃጸም ግምገማ ቢያንስ በ3 ወር 1 ጊዜ ያካሂዳሉ
- የተቀመሩ ተሞክሮዎች በክላስተሩ ተግባራዊ እንዲደረጉ ያደርጋሉ

- የጥምረቱን የአፈፃጸም መረጃ ሪፖርቶች ወቅቱን ጠብቀዉ ይልካሉ
- ከጤና ሚንስትር ከጤና ቢሮና ከአጋር አካለት የሚገኙ ሃብቶችን ለታለመለት ዓላማ ያውላሉ
- የክላስተር ንዑስ ኮሚቴ ያቋቁማሉ

የክላስተር ንኡስ ቴክኒካል ኮሚቴ

በክላስተሩ ውስጥ ካሉ ሆስፒታሎች ሆስፒታላቸውን የሚወክል አንድ ሲንየር ኤክስፐርት በማዋጣት ከ7-10 በሆኑ አባላት የሚመሰረት ሲሆን ከጥምረቱ የሚጠበቁ የቴክኒክ ስራዎች እና ተግባራት በተቀመጠው ዕቅድ መሰረት እንዲተገበር ቴክኒካል ድጋፍ ያደርጋሉ፡፡ ተጠሪነታቸውም ለክላስተሩ ይሆናል፡፡

አባል ሆስፒታሎች

በጥምረቱ ውስጥ የተለያየ አፈፃጸም ካላቸው ሆስፒታሎች ጋር በመተሳሰር ለተሻለ መማማር እና አፈፃፀም የሚሰራ ሆስፒታል ነው፡፡

የአባል ሆስፒታል የስራ ድርሻና ሀላፊነት

- በትኩረት መስኩ ላይ ከሆስፒታሉ እና ከክላስተሩ የሚጠበቁ ተግባራትን ሊያስፈጽም የሚችል እቅድ ያቅዳሉ
- ለሆስፒታሉ ሰራተኞች የአራተኛውን የትኩረት መስክ አላማ ያስተዋውቃሉ፣ እንዲተገበርም ያመቻቻሉ
- አስፈላጊ መረጃዎችን መሰብሰብ መተንተን እና ለስራ ክፍሎች ግብረ መልስ ይሰጣሉ
- በትኩረት መስኩ የሆስፒታሉ አፈፃፀሞች ወቅቱን ጠብቆ እንዲገመገሙ ያደርጋሉ
- በሆስፒታሉ የተሻሉ ልምዶችን ይቀምራሉ ያሰራጫሉ
- በክላስተሩ የተከናወኑ ተግባራትን ሪፖርት ለአስተባባሪ ሆስፒታል እና ለሚመለከታቸዉ አካላት ወቅቱን ጠብቆ ይልካሉ
- በአስተባባሪ ሆስፒታል በሚጠራው የጥምረቱ ስብሰባ ላይ በመገኘት በንቁ ሁኔታ ይሳተፋሉ፣
- ከክልል የሚቀርብለትን የተቀመሩ ጥሩ ተሞክሮዎችን ይፈጽማል ለውጡንም ይከታተላሉ፣
- የትኩረት መስኩን ተግበራዊ ማድረግ እንዲቻል ለተለያዩ ወጪዎች የሚሆን በጀት በየአመቱ ይይዛል፡፡ የሆስፒታሉን ባለሞያዎች በአራተኛው ትኩረት መስክ የተሻለ አፈፃፀም ያላቸውን ሆስፒታሎች ድረስ በመውሰድ ልምድ እንዲቀስሙ ያደርጋሉ

## ምዕራፍ 5

### የጥምረቱ 4ተኛ ዙር ወቅት የሚደረጉ አጠቃላይ የድጋፍ ማእቀፎች

በሆስፒታሎች ጥምረት ለጥራት የአራተኛ ዙር የትኩረት መስክ ተፈጻሚ ለማድረግ የሚደረጉ ድጋፎች በሶስት የሚከፈሉ ሲሆን እነዚህም፡ ቴክኒካል /Technical/፣ ፋይናንሻል /Financial/ እና የግብዓት/ቁሳቁስ /Material/ ይሆናሉ፡፡

### የቴክኒክ ድጋፍ

በአራተኛው ዙር የትኩረት መስክ ትግበራን ለማጠናከር በጤና ሚኒስቴር፣ ጤና ቢሮና አጋር አካላት የሚደረጉ አጋዥ ሰነዶች ዝግጅት (Document Preparation) ፣ ስልጠናዎች (Training) ፣ ድጋፍና ክትትል (Supportive Suppervision) ፣ ሜንተርሺፕ (Mentorship)፣ ምርጥ ተሞክሮ ማጋራት እንዲሁም የሚዘጋጁ የልምድ ልውውጥ (Experience Sharing) ፕሮግራሞችን የሚያካትት ይሆናል፡፡

- **የሰነድ/ዶክመንት ዝግጅት ድጋፍ**

  ይህ ማለት በጤና ሚንስትር ለ4ተኛው ዙር የትኩረት መስክ ለማስፈፀም የሚያግዝ አስፈላጊ የሆኑ የቴክኒክ ሰነዶች ማለትም እንደ የፕሮጀክት ሰነድ፣ መመሪያዎች፣ ስታንዳርድ፣ ቅጾች፣ ፕሮቶኮል እና ሌሎች ተዛማጅ ሰነዶች ተዘጋጅተው በሁሉም አስተባባሪ ሆስፒታሎች በኩል በጥምረቱ እንዲደረሳቸዉ ይደረጋል፡፡ ይህንን ተከትሎ አስተባባሪ ሆስፒታሎች በክላስተራቸው ሰነዱን በማስፈፀም ተግባራዊነቱን ያረጋግጣሉ፡፡

- **ድጋፍ፣ ክትትልና ሜንተርሺፕ**

  በጥምረቱ ስር የሚገኙ ሆስፒታሎች ለአራተኛው ዙር የትኩረት መስክ ላይ በጤና ሚኒስቴርና በክልል ጤና ቢሮ በጋራ ወይም በተናጠል ለአስተባባሪ ሆስፒታሎች እንዲሁም ክልል ጤና ቢሮ ከአስተባባሪ ሆስፒታሎች ጋር በመሆን ወደ አባል ሆስፒታሎች በሁሉም ዘርፍ ያልተቋረጠ ድጋፍ ይደረጋል፡፡

- **ምርጥ ተሞክሮ/ቼንጅ ፓኬጅ ማዘጋጀት እና ማሰራጨት**

  ይህ ማለት በሀገሪቷ የተለያዩ ሆስፒታሎች ያሉ ጥሩ ተሞክሮን በመቀመር ሌሎች አስተባባሪ ሆስፒታሎች እና አባል ሆስፒታሎች እንዲተገብሩት በሀርድ ኮፒ እና ሶፍት ኮፒ እንዲደርሳቸው ይደረጋል፡፡

- የልምድ ልውውጥ እንዲካሄድ መደገፍ/ማስተባበር

  ይህ ማለት አንድ አስተባባሪ ሆስፒታል/ክላስተር ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ በመሄድ ልምድ መለዋወጥ በሚፈልጉበት ወቅት መረጃ የማቅረብ እና የማመቻቸት ስራ በጤና ሚንስትር እና በክልል ጤና ቢሮ በጋራ ይሰራል፡፡

## የፋይናንስ ድጋፍ

የፋይናንስ ድጋፍ ማለት በጤና ሚኒስቴርና በክልል ጤና ቢሮ አማካኝነት ሆስፒታሎች በራሳቸው ከሚይዙት በጀት በተጨማሪ በተለያዩ ምዕራፎች ተከፋፍሎ በአስተባባሪ ሆስፒታሎች በኩል በቀጥታ የሚደረግ የበጀት ድጋፍ ነው፡፡ ይህ የበጀት ድጋፍ አራተኛው ዙር ተመርጠው ትኩረት በተደረገባቸው የአገልግሎት አይነቶች ጋር በተያያዘ ለሚከናወኑ የጥራት ማሻሻያ ፕሮጀክቶች ማስፈጸሚያ እንዲሁም በሚሰጡ መመሪያዎች መሰረት ለሌሎች የጥምረቱ ማጠናከሪያ ተግባራት እንዲውል ይደረጋል፡፡

## የማቴሪያል ድጋፍ

የግብዓት ድጋፍ ማለት በጤና ሚኒስቴርና በክልል ጤና ቢሮ በኩል የሚከናወኑ የህክምና ግብዓት ስርጭቶችና ጥገናዎች ድጋፍ ማለት ሲሆን፤ ይህም የሚከናወነው የሆስፒታሎች ትስስር (Cluster) ሪፖርት እና በተለያየ ደረጃ የሚከናወኑ ድጋፍና ክትትል ሪፖርት ግኝቶችን ማዕከል ባደረገ መልኩ የሚደረግ ድጋፍ ነው፡፡

## ምዕራፍ 6

### የጥምረቱ 4ኛው ዙር የስራ አፈፃፀም ክትትል እና የመረጃ ቅብብሎሽ ስርዓት

በሃገር አቀፍ እና በክልል ደረጃ የሚደረጉ የ4ኛው ዙር ቅንጅታዊ አሰራሮችን እንዲሁም ክላስተሮች ያሉበትን የአፈፃጸም ደረጃ የሚገመገምበት እና በተገኙ ክፍተቶች ላይ በየደረጃው ያሉ አስፈጻሚ አካላት የማሻሻያ ትግበራ የሚደረግበት ስርዓት ነዉ ፡፡

በጤና ሚንስትር ደረጃ የሚደረግ የተቀናጀ የቦታ ላይ ድጋፍ፡

በሃገር አቀፍ ደረጃ በትኩረት መስኩ ላይ በቂ ግንዛቤ ያለዉ ቡድን የቦታ ላይ ድጋፍ ለአስተባባሪ ሆስፒታሎች ያደረጋል፡፡የተቀናጀ የቦታ ላይ ድጋፉ በየ6ወሩ በያንስ ለ3 ቀናት የሚቆይ ሆኖ ድጋፉ ሲጠናቀቅ የፅሁፍ ግብረመልስም መሰጠት ይኖርበታል፡፡

በጤና ሚንስትር ደረጃ የሚደረግ የስራ አፈፃፀም ግምገማ፡

በጤና ሚንስትር ደረጃ የሚደረግ የአፈፃፀም ግምገማ በመደበኛ በሚሰበሰቡ ማስረጃዎች ላይ እና የክልል የድጋፍ ዉጤቶች ላይ መሰረት ያደረገ ሲሆን በዓመት 2 ጊዜ ይካሄዳል ለ3 ቀናት ይከናወናል፡፡ ከፌደራል እና ከክልል ከፍተኛ አመራሮች፣ የፌዴራል የቴክኒክ ቡድን አባላት፣ የአስተባባሪ ሆስፒታል ስራ አስኪያጅ እና የጥራት ክፍል ዳይሬክተር እና ሌሎች አጋር አካላት ተሳታፊ ይሆናሉ፡፡

በክልል ደረጃ የሚደረግ የስራ አፈፃጸም ግምገማ፡

በክልል ደረጃ የሚደረግ የአፈጻፀም ግምገማ እንደ ክልሉ ነባራዊ ሁኔታ የትኩረት መስኩ አፈፃፀም ከሌሎች አጀንዳዎች ጋር በጋራ ሊከናወን ይችላል፡፡

በክላስተር ደረጃ የሚደረግ የተቀናጀ የቦታ ላይ ድጋፋዊ ክትትል፡

የክላስተር ድጋፍ ለአስተባባሪ ሆስፒታሉ ሙሉ የማስተባበር ሃላፊነት የተሰጠ ሲሆን ሁሉንም አባል ሆስፒታል አሳታፊ ያደረገ መሆን አለበት፡፡ የድጋፍ ቡድኑ ከሁሉም ተቋማት በማዉጣጣት በቂ ግንዛቤ እንዲይዝ በማድረግ እና ደጋፊ ሰነዶችን በማዘጋጀት በየ3 ወሩ የሚከናወን ይሆናል፡፡ የድጋፍ ቡድኑ በ1 ሆስፒታል ለ2ቀን የሚቆይ ሲሆን ቢያንስ 7 የተለያዩ ኤክስፐርቶችን ማካተት አለበት፡፡ በትኩረት መስኮች ላይ ያሉ አፈፃጸሞችን በተሰጣቸዉ ቴምፕሌት መሰረት ሪፖርት ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡

**በክላስተር ደረጃ የሚደረግ የስራ አፈፃፀም ግምገማ፡**

**የክላስትር አፈፃጸም ግምገማ በድጋፍ ዉጤትን መሰረት በማድረግ በአስተባባሪ ሆስፒታል ሰብሳቢነት ይመራል፡ ፡ የሆስፒታል ሃላፊ፣ የድንገተና ክፍል ሃላፊ፣ የቀዶ ህክምና ክፍል ሃላፊ፣ የተመላላሽ ሃላፊ፣ የጥራት ክፍል ሃላፊ ያሳተፈ ይሆናል፡፡ በሂደቱ ቃለ ጉባኤ በመያዝ እና የድርጊት መርሃ ግብር በማዘጋጀት ለክልል ጤና ቢሮ እና ለአባል ሆስፒታሎች ይላካል፡፡ የክልል ጤና ቢሮ በስሩ ባሉ የሆስፒታል ጥምረቶች የተላከለትን ሪፖርት በመጠመር የማጠቃለያ ሪፖርት ለጤና ሚንስትር ወቅቱን ጠብቆ ይልካል፡፡ የክልል ጤና ቢሮ የጥምረቱን ሪፖርት ግብረመልስ ለአስተባባሪ ሆስፒታሎች በ1 ሳምንት ጊዜ በህጋዊ ደብዳቤ እንዲደርሳቸዉ ያደርጋል፡፡**

## ምዕራፍ 7

### የአራተኛው ዙር ማጠናቀቂያና የእውቅና አሰጣጥ ስርዓት

የጥምረቱ 4ኛዉ ዙር ማጠናቀቂያ የሆስፒታሎች አጠቃላይ የሽልማት እና እዉቅና መስጫ ፕሮግራምን ስኬታማ በሆነ መንገድ ለማከናወን የሚሰሩ ስራዎችን ያጠቃልላል፡፡

### ገለልተኛ አስተባባሪ ቡድን ማቋቋም

የትኩረት መስኩን ለማጠናቀቅ በሆስፒታሎች እና በክላስተሩ መተግበሩን በማረጋገጥ ማበረታቻ ሽልማት እና እዉቅና ለመስጠት የሚደረገው ሂደት ላይ ጉልህ ሚና የሚኖረው ቡድን ሲሆን ከጤና ሚንስትር እና ከክልል ጤና ቢሮ ዉጭ የሆኑ ከተለያዩ አጋር ድርጅቶች፤ የመንግስት መስሪያ ቤቶች የሚሰሩ ባለሙያዎች ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ የሚቋቋመዉ ቡድንም የራሱ የሆነ ዝርዝር የስራ እቅድ እና ቢጋር ይኖረዋል፡፡ የሚከተሉት ዋና ዋና ሃላፊነቶች ይኖሩታል፡-

- አጠቃላይ የሽልማት እና የእዉቅና አሰጣጥ ስርዓቱን ለማስፈጸም የሚያስችል ሰነድ እና እቅድ አዘጋጅቶ ያፀድቃል፡፡
- የሽልማት ደረጃዎችን ፤ የተሸላሚ ሆስፒታሎች ቁጥርን እና የሽልማት አይነትን አዘጋጅቶ ያፀድቃል፡፡
- የእዉቅና ፕሮግራሙን ሊያስፈፅሙ የሚችሉ የስራ ቡድኖችን ያዋቅራል፤አፈጻፀማቸዉን ይከታተላል
- በሆስፒታሎች መረጣ ሂደት እና የእዉቅና መስቻ የስራ ሂደት ላይ ለሚነሱ ማናኛዉም ቅሬታ የመቀበያ እና የመፍቻ ስርዓትን ይቀርጻል ይተገብራል፡፡

### የአመራረጥ ደረጃዎች

**የመጀመሪያ ጀረጃ ማጣሪያ**

- ይህ የአመራረጥ ደረጃ ማለት በጥምረቱ ያሉ ሁሉም ሆስፒታሎች በተለያዩ መንገዶች ወደ ጤና ሚንስትር ለሁለት ተከታታይ አመታት የሚልኩትን የስራ አፈፃፀም ሪፖርቶችን እና በአስተባባሪ ቡድኑ የሚወጡ ተጨማሪ መስፈርቶችን መሰረት በማድረግ የሚወሰን ይሆናል፡፡
- ዋና አላማዉ ፈጻሚ/ አስፈጻሚ አካላት መረጃዎችን ለውሳኔ እየተጠቀሙበት መሆኑን ማረጋገጥ ያስችላል፡፡

ሁለተኛው ደረጃ ማጣሪያ

- ይህ መረጣ ሙሉ በሙሉ በክልል የሚከናወን ሲሆን በመጀመሪያዉ የማጣሪያ ዉጤት ላይ ተመርጠዉ በጤና ሚንስትር ከተላኩ በኋላ በክልሎች እንዲያፀድቁት የሚደረግ ሲሆን ክልሎች ሚንስትር መስሪያ ቤቱ የላካቸዉን ሆስፒታሎች መቀየር አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ለተቀየሩት ሆስፒታሎች በቂ የጽሁፍ ማስረጃ በጤና ቢሮ ሃላፊ አፀድቀዉ/ፊርማ ለጤና ሚንስትር ያስገባሉ፡፡ በዚህ ወቅት ክልል የጤና ቢሮዎች መቀየር ቢፈልጉ ቢበዛ ሃያ በመቶ የሚሆነዉን ብቻ ይፈቀድላቸዋል፡፡ ዋና አላማዉም በሆስፒታል የሚላኩ መረጃዎች በተቋማት እና በክልል በኩል የተረጋገጡ፤ለዉሳኔ የሚያበቁ መሆኑን እና በየደረጃዉ ያሉ ልዩነቶችን ለማጥበብ እና በመረጣ ሂደቱ የክልል ጤና ቢሮዎችን ተሳትፎ ለማረጋገጥ ነዉ፡፡

የተሸላሚ ሆስፒታሎች የጨረሻ ዙር የስራ አፈጻፀም የቦታ ላይ የቴክኒክ ማረጋገጫ

- የመጨረሻ ዙር ማረጋገጫ በክልልም ሆነ በጤና ሚንስትር ስር ባልሆኑ ባለሙያዎች የሚከናወን ሲሆን ሂደቱም ሙሉ በሙሉ ሚስጢራዊነቱን የጠበቀ እንዲሆን ይደረጋል፡፡
- በዚህ ለ3ኛዉ ማጣሪያ የሚካተቱት ሆስፒታሎች መቶ በመቶ በ2ኛዉ ዙር ተመርጠዉ በክልል የጤና ቢሮዎች ማረጋገጫ የተሰጠባቸዉ ሆስፒታሎች ይሆናሉ፡፡

## የሽልማት እና የእውቅና መርሃግብር

በትኩረት መስኩ የመጨረሻ ማጣሪያ አልፈዉ የተሻለ አፈፃጸም ያላቸው ሆስፒታሎች እውቅና እና ሽልማት የሚያገኙበት መርሃ ግብር ነዉ፡፡ ፕሮግራሙም የፌደራል እና የክልል ከፍተኛ አመራሮች፤የተለያዩ ባለድርሻ አካላት፤ታዋቂ ሰዎች፤ ባለሃብቶች እና ሌሎች መንግስታዊ እና መንግስታዊ ካልሆኑ አጋር አካላት የሚገኙበት የ1 ቀን የሆስፒታሎች የሽልማት እና የእዉቅና መስጫ ፕሮግራም ነዉ፡፡

## Reporting format for Cluster Activity

**General information**

1. **Name of the hospital**________________________
2. **Date of ISS**______________________________
3. **Names of cluster members**

| S/No | Name of cluster hospital | Contact person | | |
|---|---|---|---|---|
| | | Name | Phone | Email |
| 1 | | | | |
| 2 | | | | |
| 3 | | | | |
| 4 | | | | |
| 5 | | | | |
| 6 | | | | |
| 7 | | | | |

4. **Names of ISS Team**

| Name | Organization | Role |
|---|---|---|
| | | |
| | | |
| | | |
| | | |
| | | |

5. **Organizational structure, senior management team composition and its major achievement in first quarter on selected 4th Cycle agendas**
6. **Availability of approved cluster plan which communicated to all member hospitals, regional health bureau and hospital governing board**

**Cluster activity**

1. **How many cluster meeting were conducted**

| Fully attended cluster members | Absence of cluster members in any meeting |
|---|---|
| | |
| | |
| | |

2. **Number of conducted site visit with their reports________________**

| Site visit | Support Areas | Major achievement | Gap identified | Action taken | Recommendation |
|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | |
| | | | | | |
| | | | | | |
| | | | | | |

3. **Potential challenges during cluster activity**

| Potential challenges | Potential challenges | Recommended solution | |
|---|---|---|---|
| | | By the cluster | |
| | | By the RHB | |
| | | By MoH | |
| | | By Partner | |

4. **Contact address of the coordinating hospital**

| Name | Email | Phone |
|---|---|---|
| Chief executive officer | | |
| Medical director | | |

## Application Form for Best Practices

**Name of originated Hospital------------------------------Completed by ---------------------------------**

**Signature -----------Phone number --------------------------- Date Send to MOH or RHB-----------**

**Title of the Best Practice**

**------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------**

**Objective of the Practice**

**-------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------**

**-------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------**

**-------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------**

**Initial Targets of the Practice**

1. **------------------------------------------------------------------------------------------------------------**
2. **--------------------------------------------------------------------------------------------------------------**
3. **-------------------------------------------------------------------------------------------------------------**

**Date at which the Practice started implementation -----------------------------------------------**

**Baseline data of the problem before the Practice**

1. **------------------------------------------------------------------------------------------------------------**
2. **--------------------------------------------------------------------------------------------------------------**
3. **-------------------------------------------------------------------------------------------------------------**

**Short summary of the best practice process**

______________________________________________________

______________________________________________________

______________________________________________________

______________________________________________________

**Current status( after practice implemented)**

1. ------------------------------------------------------------------------------------------------
2. ------------------------------------------------------------------------------------------------
3. ------------------------------------------------------------------------------------------------

**List resources used during Implementation**

----------------------------------------------------------------------------------------------------

----------------------------------------------------------------------------------------------------

----------------------------------------------------------------------------------------------------

**Estimated cost spend during implementation (in birr) -----------------------------------------------------**

**Any experience to diffuse the practice to other hospitals (Yes/NO) -----------------------**

**If yes Name of the Hospital/Hospitals Defused to ---------------------------------------------------------**

**Current status (changes brought) of the innovation practice at the above hospital/Hospitals**

----------------------------------------------------------------------------------------------------

----------------------------------------------------------------------------------------------------

----------------------------------------------------------------------------------------------------

**Thank You for your Application!!**